# የኢትዮጵያ ካባ

ቪላ ፍራይሹትስ የተሰኘው ሙዚየም በአንድ ልዩ በሆነ አውደ ራዕይ (ኤግዚቢሽን) አንድ የኢትዮጵያን ካባ ለእይታ አቅርቧል፡፡ የዚህ አይነት ከአንበሳ ጸጉር የተሰራና የተዋበ ካባ በንጉሳዊዋ ኢትዮጵያ (አቢሲኒያ) ዘመን ለታወቁ የጦር አበጋዞች በስጦታ መልክ የሚሰጥ ነበር፡፡ ይሕ ካባ በምን ያለ ሁኔታ እንደተዘረፈ በእርግጠኝነት ማወቅ ባይቻልም ካባውን ጄኔራል ኤኔያ ናቫሪኒ በአቢሲኒያ ጣሊያን ጦርነት ወቅት ከኢትዮጵያ ሜራን ወደሚገኘው ፍራይሹትስ ቪላ እንዳመጣው ወይም ይዞት እንደተመለሰ ያለጥርጥር መገመት ይቻላል፡፡

እንግዲሕ ጉዳዩ ወይም ዓውደ ራዕዩ የሚያሳየን ጦርነት፣ ድል መንሳትና ዘረፋን ነው ማለት ነው፡፡ ልብ ብሎ ላስተዋለው ይህ ካባ የሚነግረን ታሪክ የአውሮፓ ተስፋፊዎች አንድ የአፍሪካን የስልጣኔ ወይም የሐይል ማሳያ ምልክት የሆነን ነገር እንዴት አድርገው እንደሚዘረፉና የራሳቸው እንደሚያደርጉ ነው፡፡ ስለሆነም ይሕ አውደ ራዕይ ዛሬ ላይ እኛ በቅኝ ግዛት ዘመን የተዘረፉ ሐብቶችን በተመለከተ ሊኖረን ስለሚገባን እውቀትና ልንወስደው ስላለብን አቋም እንድናስብበት የሚያደርግ ጊዜ የማይሰጠው ጥያቄ ሆኖ ቀርቧል፡፡ የአውደ ራዕዩ ተመልካች ሕዝብ ይህ ሳይንሳዊና ምናባዊ ውበት የተላበሰ ሐብት ሊመለስ የሚችልበትን መንገድ እንዲያስብበምት ለማስቻል ያለመ ነው፡፡ ካባው ለኢትዮጵያ ተመልሶ ሊሰጥ አይገባምን? ይሕንን ጥያቄ ከምንሰማቸው ታሪኮችና የውርስ እሳቤዎች፣ ሰለ ታሪክ ትርክቶችና ስለውርስ እንዲሁም ስለ ማስታወሻና ተጠያቂነት የሚነሱትን ሐሳቦች ካየን በኋላ የትኛው ታሪክ ወይም ማስታወሻ ለኛ የበለጠ ተገቢና ትክክለኛ ነው የሚለውን ለማመዛዘን ይረዳናል፡፡

አውደ ራዕዩ በሐምሌ 2021 ላይ ከዚህ አለም በሞት የተለየውን የዘመኑ የታሪክ ተመራማሪ የነበረውን አንጀሎ ዴል ቦካስን ለማስታወስ ተብሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ እሱ የፋሽስት ጣሊያን ዘመን ስራዎችን በመቃወም የሰራቸው ስራዎች - በርካታ ተቃውሞዎች የገጠመው ቢሆንም - ማሕበረሰቡ ስለታሪክ ያለውን ዕይታ በዘላቂነት ለመለወጥ አስችሏል፡፡ ቢያንስ ስለሌሎች የነበራቸውን አስተሳሰብና የኛ ብለው የሚያምኑትን ታሪክ በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት በዘላቂነት እንዲለወጥ አስችሏል፡፡


Foto: Georg Tappeiner

## ከ 80 ዓመት በፊት ስለተደረገ ጦርነት

በጥር 3, 1935 በዘመናዊዋ አውሮፓ የመጀመሪያው ዲክታተር የሆነው ፋሽስቱ የጣልያን መንግስት በምስራቅ አፍሪካ ረጅም ዕድሜ ያላገኘውንና እስከ 1941 ዓመተ ምሕረት ድረስ ብቻ የዘለቀውን ኢትዮጵያን አስገድዶ ለመያዝ ጭካኔ የተሞላበትና ብዙ ደም መፋሰስ ያስከተለው ጦርነት አስከትሎ ነበር፡፡ በቤኒቶ ሙሶሎኒ የታዘዘው የጦር ወረራ በሰሜን በቅኝ ግዛት ስር ትተዳደር ከነበረችው ኤርትራና ከበስተደቡብ ከጣሊያን ሶማሊያላንድ በመነሳት በሁለት በኩል በመዝመት የተደረገ የጦር ወረራ ነበር የተፈጸመው፡፡ በመቶ ሺሕዎች የሚቆጠረው የጣልያን ጦር ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ወይም የጦርነት አዋጅ እንዲሁም ምንም አይነት ለጦርነት የሚያበቃ ምክንያት ሳይኖር ነው በድንገት በንጉስ ሐይለስላሴ አንደኛ ስር ትተዳደር የነበረችዋን የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ጥሶ ወረራ የፈጸመው፡፡ በታጠቁት ዘመናዊ የጦር መሳሪያና ባላቸው የተደራጀ አወቃቀር ፍጹም የበላይነት ከነበራቸው የተላያዩ የጦር ክፍሎች ውስጥ የተሰጠውን የወረራ ዘመቻ በመቶዎች የሚቆጠሩ የደቡብ ቲሮል የጦር ክፍሎችም ተቀላልቅለውት ነበር፡፡

በደቡብ በኩል ወረራውን የፈጸመው ጦር በበላይነት ይመራ የነበረው በሩዶልፎ ግራዚያኒ የነበረ ሲሆን ኤኔያ ናቫሪኒ ደሞ በሱ ስር ያለ የጦር መሪ ነበር፡፡ በነበራቸው ከፍተኛ የሆነ የአየር ጥቃት የበላይነትና ከፈጸሙት አሰቃቂ የጋዝ ጭፍጨፋ በኋላ ግንቦት 5, 1936 ዓ.ም የጣሊያን ወራሪ ሐይሎች የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የሆነችውን አዲስ አበባን ለመቆጣጠር ቻሉ፡፡ ግንቦት 9 ቀን 1936 ዓ.ም

ሙሶሊኒ የሰብዓዊ መብትን የጣሰውንና አለም አቀፍ ሕግን ያላከበረውን የወረራ ዘመቻ እንደተጠናቀቀ አወጀ፡፡ ኢትዮጵያን ከግዛት አንድነቱ ጋር የተቀላቀለች መሆንዋንና በምስራቅ አፍሪካ የጣሊያን ቅዝ ግዛት አካል እንደሆነች በማሳወቅ አዲሱን የሮም ሜዲትራኒያን ኢምፓየር አወጀ፡፡ በዚሁ ዕለትም የጣሊያኑ ንጉስ ቪክቶር ኤማኑኤል ሶስተኛ የአቢሲኒያ ንጉስ እንደሆነ ታወጀ፡፡ ጣልያን ጀምራው የነበረው ይህ ጨዋታ በሕዳር 1941 ዓ.ም የእንግሊዝና አሜሪካ ጥምር ጦር ከኢትዮጵያ ጦር ጋር በመሆን የጣልያንን ጦር ሙሉ ለሙሉ ድል የተመታ ሲሆን የኢትዮጵያ ንጉሳዊ አገዛዝም ተመልሶ ወደ ስልጣን እንዲመለስ ሆኗል፡፡

ይሕ በተጠና መልኩ በምስራቅ አፍሪካ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት የተፈጸመ ጭካኔ የተሞላበት አውዳሚ ጦርነትና ተግባር ለዚህ ዘመን ገደብ ያጣ ጦርነት እንደ ዘመናዊ ማሳያ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ታሪክ ነው፡፡ በጦርነቱ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የሐገሬው ሰዎች እንደሞቱና በጣም በርካቶች ደሞ ለአሰቃቂ ህይወት እንዲዳደረጉ እንደተደረገ ይገመታል፡፡ በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ከ 1936 እስከ 1941 ድረስ ባለ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘረኛ የሆነ የአፓርታይድ የአገዛዝ ስርዓት የተዘረጋ ሲሆን በዚህም የአውሮፓ ተስፋፊዎች የበላይነትንና ክብርን እንዲይዙ የተደረገ የነበረ ሲሆን የሐገሬው ሰዎች ደሞ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲገፉና እንዲገለሉ ተደርጎ ነበር፡፡ አለም አቀፉ ማሕበረሰብ ጦርነቱን በስተመጀመሪያ ላይ ያወገዘው ቢሆንም አስተላልፎት የነበረውን ማዕቀብ ብዙም ሳይቆይ በ 1936 በጋ ላይ እንዲነሳ በማድረግ በ 1941 ጣልያን ከምስራቅ አፍሪካ ሙሉ በሙሉ ድል ተነስታ እስከትወጣ ድረስ እንደልቧ እንድትዘርፍ አስችሏታል፡፡ የናዚ ፋሽስት ጦር በ 1945 ዓ.ም ከተሸነፈ በኋላም የጦር ወንጀለኞችን ለፍርድ እንዲቀርቡ ለማድረግም ሆነ በሕይወት የተረፉ የጦር ጉዳተኞችም ካሳ እንዲያገኙ የተደረገበት የሕግ ስርዓት አልተካሄደም፡፡

## ጄኔራሉ

ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት የወራሪው ጦር የጦር አዛዦች ውስጥ ጄኔራል ኤኔያ ናቫሪኒ ይገኝበታል፡፡ በ 1885 ቼሴና ውስጥ የተወለደውና በልጅነቱ ወደ ጦሩ የተቀላቀለው ናቫሪኒ በመጀመሪያው የሊቢያ ጣልያን ጦርነትና በአንደኛው የአለም ጦርነት ወቅት በወታደርነት በጦር ሜዳ ተዋግቷል፡፡ በ 1925 ዓ.ም ከሉኢዛ ፍሮም ኡ ጋር በትዳር ጓደኝነት የተጣመረው ናቫርኒ የባለቤቱ አባት ፍራንስ ፍሮም የጥበብ ስራዎችን የሚሰበስብ ሰው የነበረ ሲሆን በ 1921 ዓ.ም ቪላ ፍራይሹትስ የተሰኘውን ሕንጻ ገዝቷል፡፡ የኤኔያ እና ሉዊዛ ናቫርኒ የጋራ ልጅ የሆነችው ሮዛማሪያ በተሰጣት ኑዛዜ መሰረት በ 2013 ናቫርኒ ኡጋርቴ የተሰኘ መታሰቢያ ፋውንዴሽን ያቋቋመች ሲሆን ከዚህም በመነሳት የቪላ ፍራይሹትስ ሙዚየም ዕውን ሊሆን በቅቷል፡፡

ናቫርኒ ከ 1932 ዕስከ 1935 ድረስ ሮም ውስጥ የሚገኝ የዓንድ የጦር ትምሕርት ቤት አስተዳዳሪ ሆኖ የነበር ሲሆን በ 1936 የብርጋዴር ጄኒራልነት ማዕረግ በማግኘት የአንድ ክፍለጦር ዝቅተኛው ዕርከን ክፍል አስተዳዳሪ በመሆን ተሹሞ ነበር፡፡ በዚሁ ዓመትም በጣልያን ስር ትተዳደር ወደነበረችው ሶማሊያ በግዳጅ ሄዶ የነበረ ሲሆን በጥቅምት ወር ላይም ከዚሁ በመነሳት ነበር ለወረራ ወደ ኢትዮጵያ የሚዘምተውን ጦር ተቀላቅሎ የመጣው፡፡ በአቢሲኒያ የሐይቅ አካባቢ በመባል የሚታወቀውንና ኢርባ ሞዳ፣ ቼቤና እና ሻሸመኔ ( በወቅቱ በሸዋ ክፍለ ሐገር ውስጥ የነበረና በዓሁኑ ወቅት ደሞ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኘውን) ተራራማ አካባቢ የወራሪውን ጣሊያን ጦር እየመራ ከኢትዮጵያ የነጻነት ተዋጊዎች ጋር የተዋጋ ሲሆን፤ በተለይም እሱ የሚመራው ጦር የኢትዮጵያው ንጉስ አጼ ሐይለስላሴ አማችና የአፍሪካ የነጻነት ተዋጊዎቹ መሪ የነበሩት ራስ ደስታ ዳምጠው የሚመሩትን ጦር ገጥሞ ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ከተደረጉ ጦርነቶችና ፍልሚያዎች በኋላ በየካቲት 24 ቀን 1937 ዓ.ም ራስ ደስታ ዳምጠው የተማረኩ ሲሆን፤ ባስቸኳይ በተካሄደ የተጣደፈ ፍርድ በስቅላት እንዲቀጡ ተወስኖ በስቅላት እንዲቀጡ የተደረገ ሲሆን አስከሬናቸው እንደ ማስፈራሪያ እንዲያገለግል በማሰብ ቀኑን ሙሉ ተንጠልጥሎ ሕዝብ ሲያየው እንዲውል ተደርጓል፡፡

ከዚህም በመቀጠል ናቫርኒ ይመራው የነበረው የቅኝ ገዢው የጣልያን ጦር በወላይታ ሶዶ ሰፍሮ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የአካባቢውን ሰላም ለማስጠበቅ በሚል አላማ በመሳሪያ ሐይልና በጉልበት ብቻ ለማስፈጸም ይሞከር የነበረውን ተግባር ከማስተባበር ባሻገር መሰረተ ልማትና የመንገድ ግንባታ በዕርሱ ስር የነበሩ የስልጣን ሐላፊነቶች ነበሩ፡፡ በ 1938 ዓ.ም ከአዲስ አበባ በስተ ደቡብ ምዕራብ ላይ ወደምትገኘውና የከፋ ክፍለሐገር ዋና ከተማ ወደ ነበረችው ወደ ጅማ ተዘዋውሮም ነበር፡፡ ዕዛ ዕያለም የክፍለጦሩ አዛዥ በመሆን የማዕረግ ዕድገት አግኝቷል፡፡ በሕዳር 1938 ኢትዮጵያን ለቅቆ ወደ ጣልያን ሜራን ወደሚባል አካባቢ ተመልሷል፡፡ ከዚሕ አለም በሞት እስከተለየበት እስከ 1977 ዓ.ም ድረስም በቪላ ፍራይሹትስ ውስጥ ኖሯል፡፡

የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች፡
አሪያነ ካርበ እና ሐኔስ ኦበርማየር
ይሕንን ርዕሰ ጉዳይና አውደ ራዕዩን በተመለከተ ያላችሁን አስተያየት በሚከተለው አድራሻ ያሳውቁን፡
info@villafreischuetz.org
www.villafreischuetz.org

VILLA FREISCHÜTZ
DAS HAUSMUSEUM : LA CASA MUSEO

Euregio — Museumsjahr
Anno dei musei — Ann di
museums — 2021